

# የተጠቃሚ መመሪያ

# DC SCHOOL REPORT CARD

Get to know DC Schools. Start here.

DCSchoolReportCard.org

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR



## የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ምንድን ነው?

የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በዲስትሪክቱ ውስጥ ስለሚገኙት ሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ላይ ቤተሰቦች እንዲመለከቱ ያደርጋል። ከቤተሰቦች እና ወላጆች ጋር በህብረት ተሰርቶ፣ ይሄ መሳሪያ ተማሪዎችን የወሳኝ ውሳኔ አሰጣጥ ማዕከል ያደረገ ግልጽ፣ ፍትሃዊ የዲሲ ትምህርት ስርዓት የማስፈኛ መንገድ ነው።


የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ስለ አንድ ትምህርት ቤት ጠቅላላ መረጃ የሚያቀርብ መሳሪያ ነው፣ እና አንድ ትምህርት ቤት አፈፃጸሙ እንዴት እንደሆነ ወይም ምን ላይ መሻሻል እንደሚገባው ለማወቅ ያስችሎታል። ሁሉም ግዛቶች፣ ዲሲን ጨምሮ፣ እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን አለበት አዋጅ [Every Student Succeeds Act ወይም ኢሳ (ESSA) በሚባለው ሕግ ለቤተሰብ የሚመቹ ሪፖርት ካርዶችን በድረ ገጽ ላይ እንዲያወጡ ይጠበቅባቸዋል። የዲሲው የግዛቱ የትምህርት በላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ [Office of the State Superintendent of Education (ኦሲ) (OSSE)] የዲሲ ግዛት የትምህርት ኤጀንሲ፣ ከብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች፣ እና የማህበረሰቡ ዓባለት በሚሰጥ ግብረመልስ በመጠቀም የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድን መፍጠር ላይ ቅድሚያውን ይወስዳሉ። የሪፖርት ካርዶቹ በፌደራል ደረጃ የሚያስፈልጉ ሆነው ሳለ፣ ኦሲ (OSSE) የልጆቻቸው ትምህርት ቤት ላይ እንዲሳተፉ ለቤተሰቦች እና ለማህበረሰቡ ዓባለት ጠቃሚ የሚል ስሜት አላቸው።


ይሄ መመሪያ በ dcschoolreportcard.org ላይ የሚገኘውን የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በቅደም ተከተል ደረጃ እንዲመለከቱት ያስችሎታል። አሁንም ጥያቄዎች አለዎት? ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች የእኛን የግብዓቶች ክፍል ይጎብኙ ወይም በ DCSchoolReportCard@dc.gov ላይ ኢሜይል ይላኩልን።

## የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የሚያካትታቸው መረጃዎች ምንድን ናቸው?

የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ አንድ ትምህርት ቤት ከተማሪዎች ጋር እንዴት እንደሚሰራ እንዲያውቁ ከ150 የውሂብ ነጥብ በላይ ለወላጆች መረጃ በመስጠት ያግዛል፣ በተጨማሪም ስለ ትምህርት ቤቱ ጠቃሚ መረጃዎችን፣ የአካዳሚ መርሀግብሮች፣ በጣም የቅርብ የሆኑ የሕዝብ መጓጓዣ መንገዶች እና ከትምህርት ውጭ ያሉ አማራጭ፣ ለወላጆች እና ቤተሰቦቻቸው በዋናነት ሊያገኙት የሚገባ ሰው፣ እና ተጨማሪ መረጃዎችን ያቀርባል።

የዲሲ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ስለ ልጅዎ የአሁኑ ትምህርት ቤት አንዳንድ በጣም አንገብጋቢ ጥያቄዎችን እንዲመለስልዎ ያግዞታል። ስለ ልጆቻቸው የትምህርት ቀጣይ እርምጃ ወላጆች እና ቤተሰቦች የሚያስቡበት የመጀመሪያው ቅደም ተከተል ነው። እንደዚሁም የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ለትምህርት ቤታቸው እንዲሚገቱ ወሳኝ መረጃ ለቤተሰቦች ለማቅረብ እና ትምህርት ቤቶች አፈፃጸማቸው እንዴት እንደሆነ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ የተዘጋጀ ነው።






## ድረ ገጹን እንዴት እንደሚጠቀሙ : DCSCHOOLREPORTCARD.ORG

ኦሲ. (OSSE) የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድን ለመጠቀም በጣም ቀላል እንዲሆን ከወላጆች እና ቤተሰቦች ጋር አብሮ ሰርቷል። በ dcschoolreportcard.org ላይ የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ድረ ገጽ ላይ ሲገቡ፣ ብዙ ቁጥር ካላቸው ከሌሎች ግብዓቶች ጋር፣ ትምህርት ቤቶችን ለመፈለግ ሁለት መንገዶች ይቀርብሎታል።

1. ትምህርት ቤት ወይም የአካባቢው ትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ይፈልጉ። የትምህርት ቤቱን ወይም ትምህርት ቤቱን የሚያስተዳድር የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (ለምሳሌ፣ የዲሲ. የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ወይም ቻርተር ድርጅት) ስም የሚያውቁ ከሆነ፣ ስሙን ሲተይቡ በራስሰር የትምህርት ቤቱ ሪፖርት ካርድ ላይ ይገባሉ።

2. የካርታ ማውጫ (Mapping Tool) መሳሪያውን አሳይ። ለመዳሰስ የሚፈልጉት የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ወደ ካርታ ማውጫ (Mapping Tool) ላይ ለመሄድ ይሄንን አዝራር ይጫኑ። የካርታ ማውጫ (Mapping Tool) ለመፈለጊያ እና ትምህርት ቤቶችን ለመዘርዘር ብዙ አማራጮችን ያቀርባል።

3. የመግቢያ ቪዲዮ አጫውት። የዲስ ትምህርት ቤቶችን ከመፈለግዎ በፊት ስለ የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ? ይሄ የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ማጠቃለያ መረጃ የሚያገኙበት እና እንዴት እንደሚሰራ የሚናገር የመግቢያ ቪዲዮ ያቀርብሎታል።


4. የዲሲ. ሪፖርት አሳይ። የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአንድ ላይ አፈፃጸማቸው እንዴት እንደሚመስል ማጠቃለያ ያቀርባል። እንደዚሁም የዲሲ. ሪፖርት የብሔራዊ የትምህርት ሂደት ምዘና [National Assessment of Educational Progress (NAEP)] ውጤቶችን እና እነዚህ ውጤቶች የኦሲ. (OSSE) የረጅም ጊዜ ኢሳ (ESSA) ግቦች ላይ እንደሚደመሩ ያሳያል።

5. ለቤተሰቦች ግብዓቶች እና ለአስተማሪዎች ግብዓቶች። እነዚህ አገናኞች ቪዲዮዎችን፣ ብሮሸሮች፣ ቴክኒካል ማኑዋል እና ተጨማሪ ነገሮችን ጨምሮ ስለ ዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የበለጠ ለማወቅ የሚችሉባቸውን የተለያዩ ዓይነት ሰፊ ግብዓቶችን ላይ ይወስዶታል።

6. መረጃ አውርድ። በዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የሚቀርበው መረጃ ለማውረድ በማይክሮሶፍት ኤክሴል (Microsoft Excel) የፋይል ዕይታ ይገኛል።

7. የመገኛ መረጃ። የዲሲ. ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ላይ ጥያቄዎች አለዎት? የዚህ ክፍል ገጽ ከኦሲ. (OSSE) ጋር እንዴት ሊገናኙ እንደሚችሉ።

በሚቀጥሉት ገጾች ላይ፣ ስለ ሪፖርት ካርዱ ባህሪያት እና በገጾቹ ላይ ሊገኙ የሚችሉትን ዝርዝር መረጃዎች እንዴት እንደሚያገኙ ይማራሉ።




## ምላሽ ሰጪ የካርታ ማውጫ (MAPPING TOOL) እና ሌሎች የዳሰሳ ባህሪያቶች እና መሳሪያዎች

የትምህርት ቤቱን ሪፖርት ካርድ ትምህርት ቤቶችን ከልዩ መርሀግብራቸው፣ የሚያስተምሩት ክፍሎች፣ አካባቢ፣ እና ሌሎች የተጠቃሚ ምርጫዎች በመጠቀም መለየት የሚችል፣ ምላሽ ሰጪ በሆኑ የካርታ ማውጫ መሳሪያ በመጠቀም መፈለግ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ በሚያስተምሩት ክፍሎች፣ በትምህርት ቤት መርሀግብሮች፣ አካባቢ፣ እና የስታር (STAR) ደረጃ በመጠቀም መለየት እና ማጣራት ይችላሉ።

1. ምላሽ ሰጪ የካርታ ባህሪ። ሁሉም ትምህርት ቤቶች በካርታው ላይ ይታያሉ። በእርስዎ አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ለማየት ማጉላት ወይም በመላው ከተማ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ማጉያውን በመቀነስ ማየት ይችላሉ። የትምህርት ቤት ስም ላይ ጠቅ ማድረግ የሪፖርት ካርድ ገጽን ይከፍታል።

2. ማጣሪያዎች። የ ማጣሪያ (“Filters”) ባህሪ በትምህርት ቤት ዓይነት (ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት)፣ የሚያስተምሩት ክፍሎች፣ የሚሰጡ መርሀግብሮች እና ከትምህርት ቤት በፊት እና/ወይም ከትምህርት ቤት በኋላ አገልግሎቶች የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችን ለማወቅ ያስችላል።

3. በአድራሻ ትምህርት ቤቶችን ይፈልጉ። አድራሻ በሚያስገቡበት ሰዓት፣ የእርስዎ አድራሻ አቅራቢያ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን እንዲያዩ ይደረጋሉ።

4. ርቀት (ቅርብ ወይም ሩቅ)። ያስገቡት አድራሻ በጣም ቅርብ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ለማየት ባህሪው ያስችሎታል።

5. በክፍል ደረጃ ደርድር ይሄ ባህሪ አንድ የክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች እንዲፈልጉ ያስችሎታል።

6. አወዳድር ጎን ለጎን እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ማወዳደር ይችላሉ። ከሌላ ጋር ለማወዳደር የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት አንዴ ካገኙ በኋላ፣ አወዳድር ( “Compare”) የሚለውን አዶ ጠቅ ያድርጉ እና ለማወዳደር የዚያ ትምህርት ቤት መረጃ ለእርስዎ ይታከላል።

7. የትምህርት ቤት ሪፖርት አውርድ። የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርዱን ማጠቃለያ ለማየት የሚፈልጉ ከሆነ፣ የመረጃው ዋና ፍሬ ነገሮች የተንጸባረቁበት እና ስለ ትምህርት ቤቷ መረጃ ያለውን በቀላሉ ሊታተም የሚችለውን ፒዲኤፍ (PDF) ፋይል ለማግኘት የትምህርት ቤት ሪፖርት አውርድ የሚለውን አዝራር ይጫኑ።



## ያወዳድሩ

የዲሲ ሪፖርት ካርድ በአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ትምህርት ቤቶችን ለማወዳደር ያስችሎታል። ትምህርት ቤቶችን ለማወዳደር የሚመርጡ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ስለ እነዚህ ትምህርት ቤቶች፣ ስም የሚያስተምሩት ክፍሎች፣ የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር፣ የትምህርት ቤቱ ግልጽነት እና ሪፖርት አደራረግ [School Transparency and Reporting (STAR)] ደረጃ፣ የሚሰጡ መርሀግብሮች፣ ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ አገልግሎት ይሰጥ እንደሆነ፣ የጠቅላይ ድርጅት መረጃ፣ የተማሪ ተሞክሮ፣ እና የእገዳዎች ቁጥር በተመለከተ፥ የተለያዩ የተሰጡ ነጥቦችን ይመለከታሉ።

ለማወዳደር የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት በሚመለከቱበት ሰዓት፣ የትምህርት ቤቱ ገጽ የቀኝ ጫፍ ላይ የሚገኘውን ለማወዳደር አክል ("Add to Compare") አዶ ጠቅ ያድርጉ። ለማወዳደር ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ አንዴ ከመረጡ በኋላ፣ የድረ ገጽ የላይኛው ቀኝ ጫፍ ላይ ይሂዱ እና ጎን ለጎን የመረጧቸውን እያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች ለማየት አወዳድር ("Compare") የሚለውን ይጫኑት።

| SCHOOL NAME 1<br>Grades Served<br>0000 Students Enrolled | SCHOOL NAME 2<br>Grades Served<br>000 Students Enrolled | SCHOOL NAME 3<br>Grades Served<br>000 Students Enrolled |
|---|---|---|
| **STAR RATING** | | |
| 4 STARS | 2 STARS | 2 STARS |
| **SCHOOL PROGRAM INFORMATION** | | |
| Advanced Placement<br>Arts Integration<br>Blended Learning | Advanced Placement<br>Arts Integration<br>Blended Learning<br>Show More | Advanced Placement<br>Arts Integration<br>Blended Learning |
| **BEFORE-SCHOOL CARE** | | |
| No | Free | Free |
| **AFTER-SCHOOL CARE** | | |
| Sliding Scale/Voucher | Paid | Sliding Scale/Voucher |
| **PARENT ORGANIZATION** | | |
| Parent Organization Name | This school does not have a parent organization. | Parent Organization Name |
| **TEACHERS WITH 2+ YEARS EXPERIENCE** | | |
| 00% | 00% | 00% |
| **TOTAL SUSPENSIONS** | | |
| 00<br>per 000 students | 00<br>per 000 students | 00<br>per 000 students |

## የመግለጫ ገጽ

አንዴ ትምህርት ቤት ከመረጡ በኋላ፣ በራስሰር ወደ የትምህርት መግለጫ ገጽ ላይ ይሄዳሉ። ገጹ የሚያካትተው የትምህርት ቤቱን ማጠቃለያ፣ አካባቢ፣ የትራንስፖርት አማራጮች፣ የሚሰጧቸው ክፍሎች፣ እና ተጨማሪ ብዙ ነገሮች ያካትታል።


1. ጠቅላላ መረጃ በዚህ ክፍል ላይ፣ እንደ አድራሻ፣ ቀበሌ እና በካርታ ላይ የሚገኝበት አካባቢ፣ ስልክ ቁጥር እና ድረ ገጽ፣ የርእሰ መምህሩ ስም፣ እና የማህበራዊ ሚደያ መለያዎች ላይ አገናኝ የመሳሰሉ ጠቅላላ መረጃዎችን ያገኛሉ።

2. የትምህርት ቤቱ ማጠቃለያ እዚህ ላይ ስለሚሰጡት ክፍሎች፣ የትምህርት ቤቱ ስታር (STAR) ደረጃ፣ እና ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት፣ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ወይም ደግሞ የቻርተር ድርጅት የሆነውን የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ [local education agency (LEA)] በተመለከተ ለማወቅ ይችላሉ።


3. የወላጅ ድርጅት እና የመገኛ መረጃ ይሄ ክፍል እንደ የወላጆች ተወካይ ስም እና ኢሜይል አድራሻ፣ የወላጅ ድርጅት ስም፣ እና የወላጅ የመግባቢያ ፖሊሲ የመሳሰሉትን በትምህርት ቤት ውስጥ ወላጆች ማግኘት ያለባቸው ሰዎችን በተመለከተ መረጃ ይይዛል።

4. ከትምህርት ቤቱ መልዕክት። ይሄ ክፍል የትምህርት ቤቱ አመራር ስለ ተልዕኮው እና ምን ልዩ እንደሚያደርገው የሚናገርበትን መድረክ ይከፍታል።

5. የተማሪ ብዛት። ይሄ ክፍል በትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገቡ ጠቅላላ ተማሪዎችን ቁጥር መረጃ ያቀርባል። እንደዚሁም የተማሪዎችን ስብጥር (ለምሳሌ ተማሪዎች ብዛት በዘር/በብሔር በመቶኛ፣ በልዩ ትምህርት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፣ በኢኮኖሚ የተጎዱ ተማሪዎች፣ እና የኢንግሊዘኛ ተማሪዎች) ዝርዝር መረጃ ያካትታል።








6 የትምህርት ቤት መርሀግብሮች። ይሄ ክፍል በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ትምህርት ቤቱ ሊሰጣቸው የሚችሉ ልዩ መርሀግብሮችን ይዘረዝራል የሚያካትተውም፣ የላቀ ምደባ (Advanced Placement)፣ የአርት ውህደት (Arts Integration)፣ የተጣመረ ትምህርት (Blended Learning)፣ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (Career & Technical Education) የሁለትዮሽ የኮሌጅ ምዝገባ (Dual College Enrollment)፣ የሁለትዮሽ ቋንቋ/ ጥምረት (Dual Language/ Immersion) የተራዘመ የቀን ትምህርትት (Extended Day)፣ የተራዘመ የትምህርት ዓመት (Extended Year)፣ ኢንተርናሽናል ባቹለሬት [International Baccalaureate (IB)] JROTC፣ ሞንቲሶሪ (Montessori)፣ የድረ ገጽ ላይ ትምህርት (Online Learning) የነጠላ ጾታ ካምፓስ (Single Gender Campus)፣ ስተም ትኩረት (STEM Focus)፣ እና ኢንተርስኮላስቲክ ስፖርቶች (Interscholastic Sports)።

7 ከትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች። ይሄ ክፍል እንደ ስፖርት እና ክለቦች የመሳሰሉ ከክፍል ውጪ ለተማሪዎች የሚቀርቡ እንቅስቃሴዎችን እና አጋጣሚዎችን ይዘረዝራል።

8 የአካል እንቅስቃሴ ጊዜ። ይሄ ክፍል የሚያሰው በሳምንት ውስጥ በደቂቃ ተማሪዎች ንቁ የአካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የሚያሳልፉትን አማካኝ ጊዜ ያሳያል (ይሄ ወይም በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ወይም በእረፍት ጊዜ ላይ ያለውን ሊሆን ይችላል)።

9 ሎጅስቲኮች ይሄ ክፍል የሚዘረዝረው እንደ የትምህርት ቤት የመማሪያ ሰዓት፣ የዩኒፎርም ልብስ መስፈርቶች፣ ከትምህርት ቤት በፊት እና/ወይም በኋላ አገልግሎቶች የሚሰጡ እንደሆነ፣ እና ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት በጣም ቅርብ የሆነው የመጓጓዣ አማራጭ የመሳሰሉ ስለ ትምህርት ቤቱ ሌሎች ጠቀላላ መረጃዎችን ይዘረዝራል።

የትምህርት ቤቱ ሪፖርት ካርድ ሌሎች ክፍሎችን ለመዳሰስ፣ በመቀጠል ለመዳሰስ የሚፈልጉት ቦታ ላይ ጠቅ ያድርጉ። ስታር (STAR0 መዋቅር፣ የትምህርት አፈፃጸም፣ ወይም የትምህርት ከባቢ





## የስታር (STAR) መዋቅር

የስታር (STAR) መዋቅር ክፍል ላይ በመሄድ ቤተሰቦች ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ጥልቅ መረጃ በተመለከት በትምህርት ቤት ግልጽነት እና ሪፖርት ማድረግ [ School Transparency and Reporting (STAR)] መዋቅር ላይ ማግኘት  ይችላሉ። የስታር (STAR) መዋቅር የተማሪ ውጤት አፈፃጸም፣ የተማሪ ዕድገት፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት፣ የትምህርት ቤት ከባቢ መለኪያዎ፣ እና የማስመረቅ አቅም ላይ የትምህርት ቤቱን አፈፃጸም ለመለካት ብዙ ነጥቦችን ይጠቀማል።

ስለ ስታር (STAR) መዋቅር የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ በ dcschoolreportcard.org ላይ ግብዓቶችን ይመልከቱ።

በመዋቅሩ ውስጥ እንዴት ሁሉም ተማሪዎች አፈፃጸማቸው እንዴት እንደነበረ ከማወቅ ተጨማሪ፣ ይሄ ገጽ የእያንዳንዱን የተማሪ ብድን አፈፃጸም እንዲያዩ ያስችሎታል።  የአካለ ስንኩልነት ስላለባቸው ተማሪዎች፣ በአደጋ ላይ ያሉ ተማሪዎች፣ ኢንግሊዘኛ ተማሪዎች፣ እና እያንዳንዱን የዘር እና የብሔር ቡድን በተመለከተ ዝርዝር ውሂብ ማየት ይችላሉ። ይሄንን መረጃ ለማገኘት፣ ለመዳሰስ የሚፈልጉት ቦታ ላይ ጠቅ ያድርጉ።








# የትምህርት ብቃት

ይሄ ገጽ ስለ ትምህርት ውጤት መረጃ፣ የተማሪዎች ዕድገት፣ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት፣ ኮሌጅ እና የአካዳሚ ዝግጁነት እና የማስመርቅ ብቃት ጨምሮ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተማሪውን አጠቃላይ የትምህርት አፈፃጸም መረጃ ያቀርባል። ማየት የሚፈልጉት ክፍል ላይ ጠቅ በማድረግ እያንዳንዱ እነዚህ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝሮችን (እንደ በተማሪ ምድብ አፈፃጸም እና አገር አቀፍ አማካኝ አፈፃጸም የመሳሰሉትን) ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።


1. የተማሪ አፈፃጸም። ይሄ ገጽ የኮሌጆች እና የሥራ መስክ ስምሪት ዝግጁነት ምዘና ጥምረት [Partnership for the Assessment of Readiness for College & Careers (PARCC)] እና ባለብዙ ግዛት ተለዋጭ ምዘና [Multi-State Alternate Assessment (MSAA)] እያንዳንዱ የአፈፃጸም ደረጃ ላይ ያሉትን ተማሪዎች በመቶኛ ያሳያል።

2. የትምህርት ዕድገት። ይሄ ገጽ በ ፓርከ (PARCC) እና ኤምኤስኤኤ (MSAA) ላይ ስለ ተማሪዎች ዕድገት መረጃ ያቀርባል። ሁለት አይነት የዕድገት መለኪያዎችን ይይዛል—አንደኛው ባለፈው ዓመት ላይ ከእነሱ ጋር ተመሳሳይ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ጋር የተማሪ ዕድገት የሚያወዳድር፣ እና በተለያዩ የብቁነት ደረጃዎች ላይ አማካኝ የተማሪ ዕድገት ይመለከታል።

3. የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቁነት። ይሄ ገጽ የሚያሳየው በእንግሊዘኛ ብቃት ላይ ተማሪዎች ምን ያህል እየተሻሻሉ እንደሆነ ያሳያል። መሻሻሉ የሚመዘነው በአክሰስ (ACCESS) ለ ELLs 2.0 ፈተና በኩል ነው፣ ይሄ ፈተና ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መፃፍን ይገመግማል።

4. የኮሌጅ እና የሥራ መስክ ስምሪት ዝግጁነት ይሄ ገጽ ምን ያህል ተማሪዎች እንደሚወስዱ፣ እና ምን ዓይነት ውጤት እንዳመጡ፣ እንደ የላቀ ምደባ [Advanced Placement (AP)] እና ኢንተርናሽናል ባችሎሬት [International Baccalaureate (IB)] ፈተናዎች እና ሳት (SAT) ፈተናዎችን መረጃ ያካትታል።

5. የማስመረቅ ደረጃ። ይሄ ገጽ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መለኪያዎችን ያካትታል፥ 1) በአራት ዓመት ውስጥ የተመረቁ ተማሪዎች መቶኛ፣ 2) በአምስት ዓመት ውስጥ የተመረቁ ተማሪዎች መቶች እና 3) ምንም ዓይነት ጊዜ ቢወስድባቸውም የተመረቁ ተማሪዎችን ብዛት መቶኛ።





## የትምህርት ቤት ከባቢ

ይሄ ገጽ ስለ ትምህርት ገበታ ላይ መገኘት፣ በድጋሚ መመዝገብ፣ ደህንነት እና ሥነ ሥርዓት፣ መምህራን እና የጤና ሠራተኞች፣ እና የቅድመ ልጅነት የመማሪያ ከባቢ በተመለከተ መረጃ ያቀርባል። ማየት የሚፈልጉት ክፍል ላይ ጠቅ በማድረግ እያንዳንዱ እነዚህ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝሮችን ማግኘት ይችላሉ።


1. በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት። ይሄ ገጽ ስለ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት፣ አማካኝ የቀን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት፣ በጣም የማይቀሩ እና 90 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚያህል ጊዜ በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ምን ያህል ተማሪዎች በመቶኛ አሉ እና የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ዕድገት መረጃን ይይዛል።

2. የተማሪ ምዝገባ ለውጦች። ይሄ ገጽ የትምህርት ግማሽ ዓመት ላይ የገቡ ወይም የወጡ ተማሪዎች እንዳሉ፣ እና በትምህርት ቤት ውስጥ መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች በድጋሚ መመዝገብ ይፈልጉ እንደሆነ መረጃ ይሳያል።

3. የቅድመ ልጅነት የመማሪያ አካባቢ ይሄ ገጽ ስለ ትምህርት ቤት ክፍል አወቃቀር፣ የስሜት ድጋፍ፣ እና በቅድመ-መዋዕለ ሕፃናት ክፍሎች ውስጥ የመማሪያ ድጋፍ ሰጪዎች መረጃ ይሰጣል።

4. የትምህርት ቤት ደህንነት እና ሥነ-ስርዓት ማስከበር ይሄ ገጽ እንደ የሚታገዱ እና የሚባረሩ ተማሪዎች ቁጥር፣ እና በትምህርት ቤቱ ውስጥ የጥቃት፣ የጉልበተኝነት፣ እና የማሸማቀቅ ክስተቶችን ሪፖርት የመሳሰሉት የሥነ ስርዓት ማስከበር እና የትምህርት ቤቱ ደህንነት ጉዳዮች ላይ መረጃ ያካትታል።

5. የመምህራን እና የጤና ሠራተኞች መረጃ። ይሄ ገጽ በትምህርት ቤት ውስጥ የአስተማሪዎች የማስተማር ልምድ ድረጃ እና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የቋሚ እና የትርፍ ጊዜ የጤና ሠራተኞችን መረጃ ያካትታል።





## ተጨማሪ ነገር ከየት ማግኘት እችላለሁኝ?

አሁንም ስለ ዲሲ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ጥያቄዎች አለዎት? መልሶቹ አለን!

በራስዎ ስለ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ለማየት dcschoolreportcard.org ን ይጎብኙ። እንደዚሁም እንደ በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሪፖርት ካርዱ ላይ ባለ አንድ ገጽ መመሪያዎች እና ስታር (STAR) መዋቅር እና ተጨማሪ ነገሮች የመሳሰሉት ላይ ስለ ሪፖርት ካርዱ ተጨማሪ ግብዓቶች እና መረጃ ማግኘት ይችላሉ!

በቀረቡት ግብዓቶች፣ አስተያየቶች እና ጥቆማዎች ያልተመለሱ ተጨማሪ ጥያቄዎች ያለዎት እንደሆነ፣ በ DCSchoolReportCard@dc.gov ላይ ኢሜይል ይላኩልን።

# DC SCHOOL REPORT CARD

Get to know DC Schools. Start here.



የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በዲስትሪክቱ ውስጥ ስላሉት ሁሉም የሕዝብ ትምርት ቤቶች መረጃዎችን በእጅዎ ጣቶችዎ ላይ ያቀርባል።

## ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
## ትምህርት ቤቶች ያስሱ።
## እዚህ ላይ ይጀምሩ።

**DCSchoolReportCard.org**

osse.dc.gov | facebook.com/ossedc | @OSSEDC | (202) 727-6436

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR